## ቃሉን (ኤፌሶን 6:18) በልጆቻችን ላይ መጸለይና መደንገግ(ማወጅ)።

## Praying and decreeing the Word (Ephesians 6:18) over our children.

**ትንቢተ ኢሳይያስ 49:15** በውኑ ሴት ከማኅፀንዋ ለተወለደው ልጅ እስከማትራራ ድረስ ሕፃንዋን ትረሳ ዘንድ ትችላለችን?

አዎን፥ እርስዋ ትረሳ ይሆናል፥

እኔ ግን አልረሳሽም።

16፤ እነሆ፥ እኔ በእጄ መዳፍ ቀርጬሻለሁ፥

ቅጥሮችሽም ሁልጊዜ በፊቴ አሉ።

17፤ ልጆችሽ ይፈጥናሉ፤ (ልጆችሽ ፈጥነው ይመለሳሉ፥ your children will hurry back – GWT)

ያፈረሱሽና ያወደሙሽ ከአንቺ ዘንድ ይወጣሉ።

**ትንቢተ ኢሳይያስ 49:25** እግዚአብሔር ግን እንዲህ ይላል።
በኃያላን የተማረኩ ይወሰዳሉ፥
የጨካኞችም ብዝበዛ ያመልጣል፤
ከአንቺ ጋር የሚጣሉትን እጣላቸዋለሁ፥
ልጆችሽንም አድናለሁ።

**ትንቢተ ኢሳይያስ 54:13-14** ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፥

የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።

14፤ በጽድቅ ትታነጺያለሽ፤

ከግፍ ራቂ፥ አትፈሪምም፥

ድንጋጤም ወደ አንቺ አትቀርብም።

**ትንቢተ ኢሳይያስ 59:21** ከእርሱ ጋር ያለው ቃል ኪዳኔ ይህ ነው ይላል እግዚአብሔር፥ በአንተ ላይ ያለው መንፈሴ በአፍህም ውስጥ ያደረግሁት ቃሌ ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ ከአፍህ ከዘርህም አፍ ከዘር ዘርህም አፍ አያልፍም፥ ይላል እግዚአብሔር።

**መዝሙረ ዳዊት፥ መዝሙር 72:4** ለችግረኞች ሕዝብ በጽድቅ ትፈርዳለህ የድሆችንም ልጆች ታድናለህ፤ ከፉውንም ታዋርደዋለህ።

**መዝሙረ ዳዊት፥ መዝሙር 90:16** ባሪያዎችህንና ሥራህን እይ፥
ልጆቻቸውንም ምራ።
Let Your work appear to Your servants,
And Your glory to their children.

**መዝሙረ ዳዊት፥ መዝሙር 102:28** የባሪያዎችህም ልጆች ይኖራሉ፥
ዘራቸውም ለዘላለም ትጸናለች። The children of Your servants will continue,
And their descendants will be established before You."

**መዝሙረ ዳዊት፥ መዝሙር 112:1-2** ሃሌ ሉያ። እግዚአብሔርን የሚፈራ፥

ትእዛዙንም እጅግ የሚወድድ ሰው ምስጉን ነው።

2 ዘሩ በምድር ላይ ኃያል ይሆናል፤

የቅኖች ትውልድ ትባረካለች።

Praise the LORD!
Blessed *is* the man *who* fears the LORD,
*Who* delights greatly in His commandments.
2 His descendants will be mighty on earth;
The generation of the upright will be blessed.

**መዝሙረ ዳዊት፥ መዝሙር 115:14** እግዚአብሔር በላያችሁ፥ በላያችሁና በልጆቻችሁ ላይ ይጨምር።

**መዝሙረ ዳዊት፥ መዝሙር 127:3-5** እነሆ፥ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው፥ የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ ነው።

4 በኃያል እጅ እንዳሉ ፍላጾች፥ የጐልማስነት ልጆች እንዲሁ ናቸው።

5 ከእነርሱ ዘንድ ምኞቱን የሚፈጽም ብፁዕ ሰው ነው፤ ጠላቶቻቸውን በአደባባይ በተናገሩ ጊዜ እርሱ አያፍርም።

**ትንቢተ ኢሳይያስ 44:3** በተጠማ ላይ ውኃን በደረቅም መሬት ላይ ፈሳሾችን አፈስሳለሁና፤

መንፈሴን በዘርህ ላይ በረከቴንም በልጆችህ ላይ አፈስሳለሁ፥

**የሐዋርያት ሥራ 2:17-18** እግዚአብሔር ይላል። በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፤

ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፤

ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥

ጎበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፥

ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ፤

18 ደግሞም በዚያች ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎቼ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ ትንቢትም ይናገራሉ።

*‘ And it shall come to pass in the last days, says God,*
*That I will pour out of My Spirit on all flesh;*
*Your sons and your daughters shall prophesy,*
*Your young men shall see visions,*
*Your old men shall dream dreams.*
18 *And on My menservants and on My maidservants*
*I will pour out My Spirit in those days;*

**የሐዋርያት ሥራ 2:38-39** ጴጥሮስም። ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።

39 የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና አላቸው።

Then Peter said to them, “Repent, and let every one of you be baptized in the name of Jesus Christ for the remission of sins; and you shall receive the gift of the Holy Spirit. 39 For the promise is to you and to your children, and to all who are afar off, as many as the Lord our God will call.”

**ክብር፥ ኃይል፥ በረከት፥ ምስጋና፥ ጥበብ፥ ማዳን፥ ቅድስና፥ ውዳሴ፥ አምልኮ እጅግ በከበረ ቅዱስ ቡሩክ ዙፋኑ ላይ ላለ የእስራኤል ኃያል አምላክ የሠራዊት ጌታ፥ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንድ አምላክ ለሆነ ለእግዚአብሔር አብ ለእግዚአብሔር ለወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ለመንፈስ ቅዱስ ይሁን አሜን። ማራናታ ጌታ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የአብ ቃል የአብ ልጅ ቶሎ ና።**

ሊያደርግ የሚገባውን ያደረገ፥ የማይጠቅም ባሪያ ተረጎመው። **ሃሌ ሉያ**

http://www.shekinahworship.com , http://free.messianicbible.com/ , http://www.levitt.tv/ , http://www.choothomas.org , http://www.tribulation-now.org, http://www.thelordshour.com, http://www.divinerevelations.info/amharic, http://www.heavenvisit.com, http://www.perrystone.org